# ዝርዝረ-ተግባር፡ ለሕጻናት ማቆያ ተቋማት ኣስተዳዳሪዎች: ኮቪድ-19 የመከላከል እርምጃ

| ተግባር | ኣላስፈላጊ | ተተገበረ | ቀን | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|
| መገናኛ | | | | |
| በየመግብያውና መውጨ ስለ ኣካላዊ መራራቅ፣ ሳልን ስለመሸፈን፣ ከሙኒቲ ውስጥ ኣላስፈላጊ እንቅስቃሴዎችን ስለመቀነስ እና በተደጋጋሚ እጅ ስለመታጠብ የሚመክሩ መልእክቶች ለጥፍ | | | | |
| ከሁሉም ወላጆች፣ ሕጻናት፣ ሰራተኞችና በጎ ፈቃድ ሰራተኞች በሙሉ ቀጣይ ግንኙነት በማድረግ ራሳቸውን ጠብቀው ስርጭቱ እንዳይስፋፋ ምን እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በሚመለከት ይነጋገሩ። | | | | |
| ሰራተኞችና ወላጆች ከተቋሙ የሚገናኙበት፣ መረጃ እና ዝመናዎችን የሚያገኙበት እንዲሁም የድምጽ ስጋታቸውን የሚገልጹበት የመገናኛ ዘዴ ያዘጋጁ። | | | | |
| **ትምህርትና ዝግጅት** | | | | |
| ሰራተኞችና ወላጆችን ቀጥለው ስላሉት ርእሶች ኣስተምር፡<br>• የኮቪድ-19 ህመም ምልክቶች<br>• የእጅ ንጽሕና እና ሲስሉና ሲያስነጥሱ መሸፈን<br>• የጨርቅ የፊት መሸፈኛዎች<br>• መገለልን መቀነስ<br>ለተጨማሪ ምንጮች ኪንግ ካውንቲ ኮቪድ-19 ይጎብኙ። | | | | |
| ለኮቪድ-19 ዝግጁነትዎ በበለጠ እንዲጠናከር የኣስቸኳይ ግዜ ዕቅድዎን ይከልሱ እና ያዘምኑ። | | | | |
| በየዕለቱ የተወሰኑ ልጆችና ሰራተኞች በኣንድ ቡደን የሚሆኑበት ዕቅድ ያውጡ። | | | | |
| በየቀኑ የታመሙ ልጆች ይሁኑ ሰራተኞች የሚለዩበትና ወደቤት የሚላኩበት ሂደት በግልጽ ያስቀምጡ። (ለምሳሌ፥ ሕጻን ወላጆቹን የሚጠብቅበት ቦታ፣ ሕጻንና ወላጅ የሚያገናኝ ሰራተኛ ማን ነው?) | | | | |
| መቅረት ወይም በእንክብካቤ ወቅት የሕመም ምልክቶችን የሚያሳዩ ሕጻናትን ለመቆጣጠር እንዲረዳ የበሽተኛ ዝርዝር ቅጽ ማተም። | | | | |
| ስር የሰደደ በሽታ (ኣስም፣ ኣለርጂ. . . ወዘተ) ያለባቸው ሕጻናት የመንከባከቡ የኣስቸኳይ ግዜ ዕቅድዎ ሁሉም ሰራተኛ እንዲያውቅ ኣድርገው ይከልሱ። | | | | |
| ሰራተኞችን ስለ ጽዳት የግዜ ሰሌዳ ኣስተምሩ፡ እንዲሁም ተቋሙ ውስጥ በተደጋጋሚ ንጽሕና (ሳኒታይዝ/ዲስኢንፈክት) የሚያስፈልጋቸው ዕቃዎችና ቦታዎች ለይተው ይወቁ። "በኮቪድ-19 ግዜ የስርዓተ-ንጽሕና ለውጦች" ስለ በረኪና መሰል ፈሳሽ እና መለያዎች | | | | |
| በሕጻናት መካከል በቂ ኣካላዊ መራራቅን የሚፈጥሩ እንቅስቃሴዎች/ተግባሮች ምረጡ። | | | | |
| ሰራተኞች እንዲሁም 5 እና ከዛ በላይ ዕድሜ ያላቸው ሕጻናት ሁሌ የፊት መሸፈኛ መልበስ ኣለባቸው (በሕክምና ካልተከለከሉ በስተቀር)። ከ 2-4 ዕድሜ ያላቸው ሕጻናት ተቋምዎ ውስጥ በሚኖሩበት ግዜ የፊት መሸፈኛ ቢለብሱ ይመረጣል። ከ | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2 ዓመት በታች በሆኑ ሕጻናት የፊት መሸፈኛ አታድርጉ። | | | | |
| "ልጆች በሚመጡበት ግዜ ማጣርያ" የሲዲሲ መመርያን በመገምገም ተቋምዎ የትኞቹን ምክሮች ስራ ላይ ማዋል እንዳለበት ይወስኑ። | | | | |
| በያንዳንዱ የመግብያ ቦታዎች ለወላጆችና አጣሪ-ቡድን የሚሆን በቂ ቴርሞሜትር አዘጋጁ | | | | |

| ተግባር | ኣላስፈላጊ | ተተገበረ | ቀን | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|
| **መከላከል** | | | | |
| ከመምጣት በፊት | | | | |
| • ሰራተኞችና ልጆች በሙሉ ኪፕሚ ሆም ኢፍ ማግለል የሚለውን መመርያ መከተል ኣለባቸው።<br>ሕጻን ይሁን ሰራተኛ ሳል፣ የትንፋሽ እጥረት፣ 100.4$^{0}$F/38$^{0}$C ወይ በላይ የሰውነት ሙቀት፣ ብርድ፣ የኣፍንጫ መታፈን/ሞጭሞጫ ኣፍንጫ፣ የራስ ምታት፣ የጉሮሮ ቁስል፣ የጡንቻ ወይም የኣካል ሕመም፣ ድካም፣ ማቅለሽለሽ/ማስታወክ፣ ተቅማጥ፣ ኣዲስ የተከሰተ የጣዕም ወይም የማሽተት እጦት ወይም ሌላ ቀድሞ ከነበረ ሕመም ግንኙነት የሌለው ኣዲስ ምልክት (እንደ ወቅታዊ ኣለርጂ) ካሳዩ እቤት መቆየት ኣለባቸው። ወቅታዊ የኮቪድ-19 በሽታ ዝርዝር ምልክቶች ለማየት ይህንን የሲዲሲ ኮቪድ-19 ምልክቶች ይጎብኙ። | | | | |
| ወላጆች/ኣሳዳጊዎች ወደ ማቆያ ተቋም ከመምጣታቸው በፊት የልጆቻቸው የሰውነት ሙቀት እንዲለኩ ጠይቁ። | | | | |
| ሰራተኞች ወደ ማቆያ ተቋም ከመምጣታቸው በፊት የሰውነታቸው ሙቀት እንዲለኩ ጠይቁ። | | | | |
| በመምጫ ሰዓት ከወላጆች/ኣሳዳጊዎች እና ልጆች 6ጫማ ርቀው ይቁሙ (ካልተቻለ ሲዲሲ በሚመክረውን መመርያ መሰረት የመከላከያ መሳርያ (PPE) በመልበስ): የሚከተሉትን እርምጃ ይውሰዱ፣ | | | | |
| ወላጅ/ኣሳዳጊ ወደ ተቋም ከመምጣታቸው በፊት የልጃቸውን የሰውነት ሙቀት ለክተው እንደሆን ይጠይቁ<br><br>**ከቤት ሳይወጡ የሰውነት ሙቀት የለኩ እንደሆን** የወላጅ የቴምፕረቸር<br><br>ሪፖርትን ይዘግቡ።ሴ<br>• | | | | |
| • **የሰውነት ሙቀት እቤት እያሉ ካልወሰዱ** ወላጅ/ኣሳዳጊ በመግብያ ቦታ እያሉ የልጃቸውን ሙቀት እንዲለኩ ይጠይቁ። የቴርሞሜትር መመርያ እታች ተዘርዝረዋል። (ወላጅ/ኣሳዳጊ ሙቀት በሚለኩበት ግዜ ሰራተኞች የ6ጫማ ኣካላዊ ርቀት መጠበቅ ኣለባቸው) | | | | |
| ማንኛውም ወላጅ/ኣሳዳጊ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሾቹን ዘግቡ።<br>• ልጅዎ እታች ከተዘረዘሩት ምልክቶች ኣንዱ ኣለበት?<br>o ሳል<br>o የትንፋሽ እጥረት<br>o የሰውነት ሙቀት100.4$^{0}$F/38$^{0}$C ወይ በላይ | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| o የኣፍንጫ መታፈን ወይ ሞጭማጫ ኣፍንጫ<br>o የራስ ምታት<br>o የጡንቻ ወይም የሰውነት ሕመም ወይም ብርድ<br>o የጉሮሮ ቁስል<br>o ድካም<br>o ማቅለሽለሽ፣ ማስታወክ ወይም ተቅማጥ<br>o ኣዲስ የመቅመስ ወይም የማሽተት እጦት<br>o ወይም ቀድሞ ከነበረ ሕመም ግንኙነት የሌለው ሌላ ኣዲስ ምልክት፡ (እንደ ወቅታዊ ኣለርጂ)<br>• ልጅዎ ከቪድ-19 እንዳለበት ከተረጋገጠ ሰው የቅርብ ግንኙነት ኣድርገዋልን?<br>• ልጅዎ ወደ ማቆያ ተቋም ከመምጣቱ በፊት የትኩሳት ማስታገሻ መድሃኒት ወሰደ?<br>• ልጅዎ ባለፉት 10 ቀናት ውስጥ የኮቪድ-19 ምርመራ ወስዶ ኣዎንታ ውጤት ኣገኝተዋል (የኣክቲቭ ቫይረስ)?<br>• ባለፉት 14 ቀናት፡ የህዝብ ጤና ወይም የጤና ባለሞያ ስለ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ በመስጋት፡ ልጅዎን እንዲከታተሉ፣ ለብቻ እንዲያደርጉ፣ ወይም ከሌሎች እንዲርቅ ነግሮዎታል?<br><br>እላይ ካሉት ጥያቄዎች ኣንዱም ቢሆን "ኣዎ" የሚል መልስ ካገኙ ልጁ ወደ ተቋሙ መግባት የለበትም። | | | | |
| **ተግባር** | **ኣላስፈላጊ** | **ተተገበረ** | **ቀን** | **ፊርማ** |
| ቀኑን ሙሉ | | | | |
| ሕጻናት የሕመም ምልክት ያሳዩ እንደሆነ በዓይን ይቃኙ። ምልክቶቹ እንደ የጉንጭ ቀለም መቀየር፣ ፈጣን መተንፈስን ወይም የመተንፈስን ችግር (ኣለምንም ኣካላዊ እንቅስቃሴ፣ የሰውነት ድካም ወይም ከተለመደው ባህርይ ውጭ ማሳየት። | | | | |
| የማቆያ ተቋም ሰራተኞች ሕጻናቱ ምልክት ማሳየት ጀምረው እንዳይሆን የሰውነታቸውን ሙቀት ይለኩ። | | | | |
| ሰራተኞች ምልክት ማሳየት ጀምረው እንዳይሆን የገዛ ራሳቸው ሙቀት ይለኩ። | | | | |
| **ሰራተኞች የሰውነት ሙቀት መለካት ከፈለጉ ተዘጋጅቶ የቀረበ የቴርሞሜተር መመርያ ይከተሉ, የሚከተሉትንም ጭምር፥**<br>• ከተቻለ ኣለንክኪ፡ ልጆቹን ሳይነኩ ከሩቁ የሰውነት ሙቀት የሚለካ፡ ቴርሞሜተር ተጠቀሙ።<br>• ኣለንክኪ ቴርሞሜተር ከተጠቀሙ ጓንት መልበስ/እጅ መታጠብ/የእጅ ንጽህና ልምዶች ኣስፈላጊ ኣይደሉም። | | | | |
| እንደ ዲጂታል ቴርሞሜተር እና የግንባር ስካነር የመሳሰሉ የንክኪ ቴርሞሜተር እየተጠቀሙ ከሆነ በተቻለ መጠን ጓንት ይልበሱ። የሕጻናት የሰውነት ሙቀት በሚለኩበት ግዜ ጓንት ከመልበስ ፈንታ እጅን በሳሙና መታጠብ ወይም ሳኒታይዘር መጠቀም ይቻላል። ኣለንክኪ ካልሆነ በስተቀት ቴርሞሜተሩ ኣንዴ ተጠቅመን እንደገና ከመጠቀማችን በፊት ዲስ-ኢንፈክት ማድረግ ኣለብን። | | | | |
| ተቋምዎ ደጋግመው የሚያጸዱበትን ብዛት በመጨመር ሶስቱ የ ማጽዳት፣ ማለቅለቅ፣ ሳኒታይዝ/ዲስ-ኢንፈክት እርምጃ ይከተሉ 1. ማጽዳት 2. ማለቅለቅ እና 3. | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሳኒታይዝ/ዲስኢንፈክት። ለተጨማሪ በኮቪድ-19 የማጽዳትና ዲስኢንፈክት ማድረግ ሰነድ ይጎብኙ። | | | | |
| በረኪና (Bleach) ካልሆነ በስተቀር ለጽዳት የሚጠቀሙበት ኬሚካል የጥቅም ፈቃድ (ላይሰንስ) ያለበት መሆን ኣለበት። ጸረ ኮቪድ-19 ቫይረስ ተብለው በ EPA የጸደቁ የጽዳት ምርቶች ዝርዝር እዚህ ማግኘት ይቻላል። | | | | |
| ሳሙና/ውሃ/የወረቀት ፎጣ ወይም የእጅ ሳኒታይዘር (60% ኣልኮሆል) ያለበት የእጅ የንጽህና ጣብያዎች ያዘጋጁ። ጣብያዎቹ ከህንጻ ውጭም ማዘጋጀት ኣለብዎት። | | | | |
| የእጅ ሳኒታይዘr በልጆች ላይ በሚጠቀሙበት ግዜ፡<br>• በሕጻኑ ላይ ከመጠቀማችን በፊት ዓመታዊው የፈቃድ ቅጽ በወላጅ/ኣሳዳጊ መሞላቱን ማረጋገጥ ኣለብን።<br>• ከ2 ዓመት ዕድሜ በታች በሆኑ ሕጻናት መጠቀም የለብንም። | | | | |

የስያትልና ኪንግ ካውንቲ ህዝብ ጤና መመርያ የኣካባቢያችንን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የህብረተሰቡን ጤናና ደህንነት ለመጠበቅ ያለን ቁርጠኝነት ያንጸባርቃል። ከየኣካባቢው፣ ከስተይት እንዲሁም ከብሔራዊ ተቋማት የሚወጡ መመርያዎች የተለያዩ መሆናቸውን ተገንዝበው ይሆናል።

# ዝርዝረ-ተግባር ለሕጻናት ማቆያ ተቋማት ኣስተዳዳሪዎች:
# በተቋምዎ የተረጋገጠ ወይም የተጠረጠረ የኮቪድ-19 ኬዝ በሚኖርበት ግዜ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች

| ተግባር | ኣላስፈላ | ተተገበረ | ቀን | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|
| **ሰው ሲታመም መደረግ ያለበት** | | | | |
| **በማቆያ ተቋም እያሉ ሕጻናት ወይም ሰራተኞች የሕመሙ ምልክት ካሳዩ** | | | | |
| ኪፕ ሚ ሆም ኢፍ የሚለውን የማግለል መመርያ ይከተሉ | | | | |
| ሕጻን ወይም ሰራተኛ በሳል ፣ በአተነፋፈስ ፣ በ 100.4°F / 38°C ወይም ከዚያ በላይ የሙቀት መጠን ካለ ፣ ብርድ ብርድ ማለት ፣ መጨናነቅ ወይም የአፍንጫ ፍሳሽ ፣ የራስ ምታት፣ የጉሮሮ ቁስል፣ የጡንቻ ወይም የአካል ሕመም፣ ድካም፣ ማቅለሽለሽ/ማስታወክ፣ ተቅማጥ፣ ኣዲስ የተከሰተ የጣዕም ወይም የማሽተት እጦት ወይም ሌላ ቀድሞ ከነበረ ሕመም ግንኙነት የሌለው ኣዲስ ምልክት (እንደ ወቅታዊ ኣለርጂ) የመሳሰሉ ምልክቶች ካሳዩ ከታች ያሉ እርምጃዎችን ይከተሉ። | | | | |
| ምልክት ላሳዩ ግለሰቦች የበሽተኛ ዝርዝር ቅጽ ይሞሉ። | | | | |
| ለታመመ ልጅ | | | | |
| የታመመው ልጅ የወላጅ/ኣሳዳጊ መምጣት በሚጠባበቅበት ግዜ ልጁን የሚንከባከብና የሚቆጣጠር ሰራተኛ ይመድቡ። | | | | |
| የታመመው ልጅ ከሰራተኞችና ከሌሎች ልጆች የሚለይ ሰራተኛ ይመድቡ። የሚቻል ከሆነ የታመመው ልጅ ሰው በሌለበት የማቆያ ክፍል ሆኖ ወላጅ/ኣሳዳጊ መጥተው እስኪወስዱት እንዲጠብቅ ያድርጉ። | | | | |
| ከተቻለ፡ ልጆቹን በሙሉ የታመመው ልጅ ካለበት (ብዙ ግዜ ከፈጀበት) ክፍል በማስወጣት ነጻ ወደሆነ ክፍል ይውሰዱ። የታመመው ልጅ የተጠቀመባቸው በታዎች በሙሉ ሌሎች እንዳይገቡበት/እንዳይጠቀሙበት ይዝጉ። | | | | |
| የተመደበው ሰራተኛ የታመመውን ልጅ በሚንከባከብበት ግዜ የሕክምና ደረጃ ማስክ መልበስ ኣለበት። የታመመው ልጅ ከ 2 ዓመት ዕድሜ በላይ ከሆነ የፊት መሸፈኛ/ማስክ መልበስ ኣለበት። የተመደበው ሰራተኛ ልጁ የፊት መሸፈኛ/ማስክ በደምብ እንዲለብስ መርዳት ኣለበት። | | | | |
| የልጁን ወላጅ/ኣሳዳጊ ኣሳውቅ። በተቻለ መጠን ቶሎ ብለው ልጃቸውን እንዲወስዱ በትሕትና ይጠይቁ። | | | | |
| ልጁን ለመንከባከብ የተመደበው ሰራተኛ፡ ወላጅ/ኣሳዳጊ እንደመጡ፡ ልጁን ወደ ተቋም መግብያ በታ ኣጅቦት ይሂድ። | | | | |
| ወላጆች የልጃቸውን ሓኪም ጋር በመደውል ለኮቪድ-19 እንዲመረመር ወይም ወደ ነጻ የምርመራ ጣብያ እንዲወስዱ ይምከሩ። | | | | |
| ለታመመ ሰራተኛ | | | | |
| የታመመው ሰራተኛ ከልጆችና ከሌሎች ሰራተኞች ይለዩ። የታመመው ሰራተኛ ወደቤት እንዲሄድ ያድርጉ። | | | | |
| የታመመው ሰራተኛ ፒክ የሚያረጋቸውን ሰው እስኪመጣላቸውና በተቋሙ ውስጥ እስካሉ ድረስ፣ ወይም ህዝባዊ መጓጓዣ የሚወስዱ ከሆነ የፊት መሸፈኛ/ማስክ እንዲለብሱ ይምከሩ። | | | | |
| የታመመውን ሰራተኛ ፒክ የሚያረጋቸው ሰው እየጠበቁ ከሆነ፡ በተቻለ መጠን ነጻ በሆነ ክፍል ለብቻ ሆነው እንዲቆዩ ይደረግ። | | | | |
| የታመመው ሰራተኛ ሓኪማቸው ጋር እንዲደውሉና የኮቪድ-19 ምርመራ | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| እንዲያደርጉ ወይም ወደ ነጻ የምርመራ ጣብያ እንዲሄዱ ይምከሩ። | | | | |

| ተግባር | ኣላስፈላ | ተተገበረ | ቀን | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|
| የታመመው ሰው በታው እንደለቀቀ ማጽዳት እና ዲስኢንፈክት ማድረግ | | | | |
| የታመመውን ልጅ ሲንከባከብ የቆየው ምድብ ሰራተኛ፥<br>1. እጅ መታጠብ<br>2. ልብስ መቀየር፣ ልብሱ እስኪታጠብ በላስቲክ ከትቶ ማሸግ<br>3. የፊት መሸፈኛ በማውለቅ ፕላስቲክ ባለበት የቆሻሻ መጣያ መክተት ወይም እንኪታጠብ በፕላስቲክ ማሸግ።<br>4. እንደገና እጅ መታጠብ።<br>5. ኣዲስ የፊት መሸፈኛ መልበስ | | | | |
| የታመመው ልጅ የተጠቀመባቸው የጨርቅ ዕቃዎች እንደ ብርድ ልብስ፣ ኣንሶላ እንዲሁም መጫወቻዎች በፕላስቲክ ውስጥ ኣስገብቶ ማሸግ፡ ቆይቶም ላውንድሪ ውስጥ ማጠብ። | | | | |
| የታመመው ግለሰብ ግዜ ያጠፋባቸው ክፍሎች በሙሉ መጽዳትና ዲስኢንፈክት መደረግ ይኖርባቸዋል። ስለ ተገቢ የበረኪና (Bleach) ኃይል እና ኣጠቃቀም ለማወቅ በኮቪድ-19 የማጽዳትና ዲስኢንፈክት ማድረግ ሰነድ ይከተሉ።<br>• በቂ የኣየር ዝውውር እንዲኖር ወደ ውጭ (outdoor) የሚያገናኙ የክፍሎቹ በሮችና መስኮቶች ይክፈቱ።<br>• ማጽዳትና ዲስኢንፈክት ማድረግ ከመጀመርዎ በፊት በተቻለ መጠን የታመመው ግለሰብ ክፍሉን ለቆ ከወጣ 24 ሰዓት ወይም ተግባራዊ የሆነ ግዜ ይጠብቁ። | | | | |
| ለተጨማሪ መረጃ ለህጻናት ማቆያ ተቋማት ኣስተዳዳሪዎች መመርያ፡ በተቋምዎ ውስጥ የተረጋገጠ ወይም የተጠረጠረ የኮቪድ-19 ኬዝ ሲከሰት ምን ማድረግ እንዳለብዎት ይጎብኙ። | | | | |
| **መገናኛ** | | | | |
| ስለተከሰተው የተረጋገጠ ወይም የተጠረጠረ የኮቪድ ኬዝ የተቋሙ ኣስተዳዳርን ኣሳውቅ። | | | | |
| የሚወሰድ እርምጃን ለማስተባበር ወሳኝ የሆኑትን ሰራተኞች፡ መምህራን፡ የጽዳት ሰራተኞች፡ የኣመራር ኣካላትም ጭምር ኣነጋግር። | | | | |
| የተረጋገጠ የኮቪድ-19 ኬዝ ካለው ግለሰብ የቅርብ ግንኙነት ያደረጉ ልጆች ካሉ፡ የኮቪድ-19 **የተጋላጭነት ማረጋገጫ ደብዳቤ** በማዘጋጀት ወላጆቻቸውን ኣሳውቁ። | | | | |
| ካስፈለገም ለሰራተኞችና የቅርብ ግንኙነት ላልነበራቸው ልጆች ወላጅ፡ ለመረጃ ብቻ የሚያገለግል የኮቪድ-19 የእውነታ ገጽ ቅጂ መስጠት ይችላሉ። | | | | |
| ኣስታውሱ፡ የታመመውን ወይም የተጠረጠረውን ግለሰብ ለይቶ ሊያወጣ የሚችል መረጃ ከሌሎች ቤተሰቦች ኣትጋሩ። | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የሚቀጥሉት ካጋጠሙ እባክዎን **ሕዝብ ጤናን ያሳውቁ፡**<br>• በተቋምዎ ውስጥ ቆይታ ካደረጉ ግለሰቦች አንድ ወይም ከአንድ በላይ ለኮቪድ-19 ተመርምረው አዎንታዊ ውጤትካገኙ፡<br>• **ወይም፡** በተቋምዎ ከሚገኙ ሁለት ወይም ከዛ በላይ ልጆች ወይም ሰራተኞች የኮቪድ-19 ምልክት ካሳዩ፡<br>የሕዝብ ጤና ባለስልጣን ለማሳወቅ፥<br>• የኮቪድ-19 የስልክ ጥሪ ማእከል 206-477-3977 ከጥዋት 8:00 AM እስከ 7:00 PM ባለ ግዜ ይደውሉ። ምርጫ 3 ይምረጡ። እባክዎን የሕጻናት ማቆያ ተቋም ባልደረባ መሆንዎን ያሳውቁ። አስተርጓሚ ካስፈለገ ይቀርብልዎታል።<br>**ወይም**<br>• ወደ **ኦንላይን ቅጽ** በመሄድ **የኮቪድ-19 መመዝገብያ ዳሰሳ** ይምሉ። የህዝብ ጤና በስልክ ወይም በኢመይል መልስ ይሰጥዎታል። | | | | |
| ፈቃድ (ላይሰንስ) የሰጥዎትን አካል አዎንታ ኬዝ እንደተከሰተ ያሳውቁ። | | | | |
| ለተወሰነ ግዜ ተቋሙን ለመዝጋት እያሰቡ ከሆነ፡ | | | | |
| የኮቪድ-19 የስልክ ጥሪ ማእከል 206-477-3977 ከጥዋት 8:00 AM እስከ 7:00 PM ባለ ግዜ ይደውሉ። ምርጫ 3 ይምረጡ። እባክዎን የሕጻናት ማቆያ ተቋም ባልደረባ መሆንዎን ያሳውቁ። አስተርጓሚ ካስፈለገ ይቀርብልዎታል። | | | | |

የስያትልና ኪንግ ካውንቲ ህዝብ ጤና መመርያ የአካባቢያችንን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት የህብረተሰቡን ጤናና ደህንነት ለመጠበቅ ያለን ቁርጠኝነት ያንጸባርቃል። ከየአካባቢው፣ ከስተይት እንዲሁም ከብሔራዊ ተቋማት የሚወጡ መመርያዎች የተለያዩ መሆናቸውን ተገንዝበው ይሆናል።